# በፌስቡክ መድረካችን ላይ ለቀረበ ጥያቄና ለተሠነዘረ ትችː
# ከኢትዮጵያː የእግዚአብሔር መንግሥት የተሰጠ መልስ።

**፩ኛː ከItyoppiya Utopia** የቀረበ ጥያቄ፦

*"እባክህ በይበልጥ አብራራልንː ከስማቸው በቀር እንዴት እነዚህ ኹለት ግለሰቦች የድንግል ማርያም አሰራር ሊሆኑ ይችላሉ?"*

**ከኢእመ የተሰጠ መልስ፦**

ከኹሉ አስቀድሞː "ኢትዮጵያː የእግዚአብሔር መንግሥት" ማን እንደኾነች ማሳወቁና ማወቁ አስፈላጊ ይኾናል። ይህንምː "እርሷማː የእግዚአብሔር አብ መርዓት [ሙሽሪት=ሚስት] እና የልጃቸውː የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ እናት፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም አሥራፂ የኾነችውː እግዚአብሔር እምː ድንግል ማርያም ናት።" በሚል አጭር ቃል ይገልጧል።

እርሷምː ከንጉሠ-ነገሥቱና ከሊቀ-ሊቃነ-ካህናቱ ልጇ ጋርː በፈጣሪነቷና በንግሥትነቷ፥ በአገርነቷና በመንግሥትነቷምː በምድር ብቻ ሳይኾንː በሰማይም በሚገኙ ፍጥረታተ-ዓለማት ላይ ኹሉ ሰፍናː ርኩሳን መናፍስት [ሰይጣናት] እና ክፉዎች ሰዎች [የዓለሙ ሕዝቦች]ː ከእግዚአብሔራዊው ሥርዓት ውጪː በእየራሳቸው ፍላጎትና ምርጫː በተለያየ ስያሜና ዓላማ፥ መልክና ይዘትː "አገራችን፥ ግዛታችን" እያሉː በወሰኗቸው የምድርና የባሕር ክልሎቻቸው ውስጥː ያቋቋሟቸውንː የአገዛዝ ድርጅቶችː በቍጥጥሯ ሥር አድርጋː በበላይነት የምትመራና የምታስተዳድር፥ የምትመግብና የምትጠብቅ ናት።

"መንግሥት" የሚባለው አቋምና ስም አጠራሩː የዓለማቱና የፍጥረታቱ ፈጣሪና ባለቤት የኾነውː የእግዚአብሔር ብቻ ስለኾነː ይህ ተቋምና ስያሜውː ለርኩሳኑ መናፍስትም ኾነː ለሰብአውያኑ ክፉዎች ፍጡራን አገዛዝː ሊሰጥ አይቻልም። በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ-ቅዱስ የአምልኮ ሥርዓት የሚመራና የሚካኼድ እምነትና ምግባር ያላቸውː ንጉሥና ንግሥት የሚያስተዳድሩትና የሚያገለግሉት፥ የሚመግቡትና የሚጠብቁት፥ የሚቆጣጠሩትና የሚንከባከቡትː ሕዝባዊ ሕይወት ብቻ ነውː "መንግሥት" የሚባለው። ከዚህ ውጭː ተቃራኒ ኾኖ የተቋቋመና የሚቋቋም ድርጅት ኹሉː "አገዛዝ" ይባላል።

ቀድሞ፥ ዛሬና ወደፊትምː በመላው ዓለም ሕዝቦች ላይː በእግዚአብሔር እውነት ጸንቶː ሲሠራ የኖረውና የሚኖረውː ይህː እግዚአብሔራዊው ሥርዓት ነው።

ስለዚህ፡ "ኢትዮጵያ" በሚለው ስሟ በሚጠራው አገር፡ የሚኖረውን ሕዝብ፡ ለዚህ ለተነሣንበት ዓላማችን፡ ምሳሌ አድርገን ብንጠቀምበት፡ ለቀረበው ጥያቄ፡ በቂ መልስ የኾነውን እውነታ፡ በቀላሉ ልናገኝ እንችላለን።

ይኸውም፡ ይኸው የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ ገና፡ በሥነ-ፍጥረት መጀመሪያ፡ የተመሠረተበትን፡ እግዚአብሔራዊዉን የመንግሥት ሥርዓት ባለመፈለግ፡ ከዚያ ውጭ፡ በየዘመናቱ፡ በራሱ ዝንባሌ፥ ወይም፡ በባዕዳን አምልኮና ፍልስፍና እየተማረከ፥ በክፋት አገዛዝ የመኖር ፍላጎቱንም እያሳየና እየመረጠ በኼደ መጠን፡ ይህ ድርጊቱ፡ የእናቲቱ፡ የቅድስት ድንግል ማርያም እና የልጇ የኢየሱስ መሲሕ የኾነችውን፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን፡ በቅድሚያ፡ በሥውር፥ በመጨረሻም፡ በግልጽ ክህደትና ዓመፅ፥ ክፋትና የአምልኮ አመንዝራነት፡ "አልፈልግም!" ብሎ በመቃወም፡ ራሱን፡ ከኢትዮጵያዊ ማንነቱ እንዲለይ ከተገደደበት ውሳኔው ደርሶ፡ እነሆ ዛሬ ለሚገኝበት አሳዛኝና አሳፋሪ ኹኔታው መዳረጉ ነው።

ይህንኑ ሕዝብ፡ ለዚህ ውሳኔ ያደረሰው፡ የፈለገውን ዓይነት የእምነትና የምግባር፥ የሕይወትና የአኗኗርም ወግ፡ ለመምረጥና ለመቀበል፥ ለመከተልና በተግባር ላይ ዐውሎ ለመፈጸም፡ ጥንቱኑ፡ ከፈጣሪው፡ በተፈጥሮ የተሰጠው፡ ያ፡ ፍጹሙ እግዚአብሔራዊ ዕውቀትና ነጻነት፥ ሥልጣንና ኃይል መኾኑ ሊታወቅ ይገባል።

በዚህ መሠረት፡ ሕዝቡ፡ በደርግ ዘመንም ኾነ፥ አኹን በኢሕአዴግ ጊዜ፡ "ለዚያው ፍላጎቱና ምርጫው ተዳረገ!" ማለት ነው። አዎን! "ያን ዓይነቱን፡ የፈለገውንና የመረጠውን አገዛዝ ማግኘት ብቻ ሳይኾን፡ አገዛዙን፡በራሱም ላይ የሚያስፈጽሙ ገዢዎች ተሰጡት!" ማለት ነው።

እንደሕዝቡ ፍላጎትና ምርጫ፡ አገዛዙን የሚያስፈጽሙ፡ እነዚያን፡ የደርጉንና እነዚህን የኢሕአዴግን ገዥዎች፡ በሥልጣኑ ዙፋን ላይ ያስቀመጠችላቸው፡ ማን ትመስላችኋለች? ከልጇ ጋር፡ ራሷ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ ድንግል ማርያም ናት እኮ። በአላዋቂነት ቀንበር ተጠምደው ለሚኖሩትና ማናቸውም ዓይነት መለኮታዊ መልእክት ሊገባቸው ያልቻሉ ሰነፎች፡ ይህን እውነታ፡ እንዲገነዘቡት ለማድረግ፡ የተቀደሰ ስሟን አንግበውና ተሸክመው፡ እንደሕዝቡ ፍላጎትና ምርጫ፡ አገዛዛቸውን፡ በሕዝቡ ላይ ሊፈጽሙና ሊያስፈጽሙ፡ ከእርሷ የበላይ መንግሥትነት የተቀበሉትን ተልእኳቸውን፡ በዚሁ፡ በከሃዲውና በዓመፀኛው፥ በክፉውና በኣመንዛሪው ትውልድ ላይ ያካኼዱትና የሚያካኺዱት ፀረ-እግዚአብሔር እና ፀረ-ማርያም ግለሰቦች፡ ይኸውላችሁ ተመልምለው ተመደቡ።

እንግዴህ፡ የምሥጢሩ ማብራሪያ ፍቺ፡ አንዱ ዘርፍ ይኼ ነውና፡ እንድትረዱት ይኹን። የምትረዱትም፡ ለዲያብሎሳዊው ሓሰት ተገዢ በኾነው፡ በሥጋዊው አእምሮአችሁ አይደለም፤ ለእግዚአብሔራዊዋ እውነት ታማኝ በኾነው፡ በመንፈሳዊው አእምሮአችሁ ነው እንጂ። በአንድ ወገን ስማቸው፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ ሰውነታቸው፡ ለምን ለምን ተልእኮ [መልእክታዊ አገልግሎት] እንደተፈለገ፣ ከማብራሪያው፡ በቀላሉ ለመረዳት እንደቻላችሁ እንተማመናለን።

**፪ኛ ከDeneke Tadesse የተሠነዘረ ትች፦**

*ቃለ ህይወት ያሰማልን። ማስተካከያ:-አባ ሀርያቆስ ኢትዮጵያዊ ሳይሆኑ ግብጻዊ ናቸው።*

**ከኢእመ የተሰጠ መልስ፦**

በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ የቅዳሴ ማርያም ደራሲ፡ ገዳማዊ ሕርያቆስና የውዳሴ ማርያም ደራሲ፡ ቅዱስ ኤፍሬም፥ እነርሱን የመሰሉት ኹሉ፡ እንደኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ፡ "ኢትዮጵያውያን" መኾናቸውን አያውቁምን?

ኢትዮጵያዊው፡ የጋሥጫው ገዳማዊ ጊዮርጊስ እንደደረሳት፡ እንደመዓዛ ቅዳሴ ማርያም ኹሉ፡ የቀሩት፡ ፲፩ቱም የቅዳሴ መጻሕፍት፡ የኢትዮጵያ መኾናቸውን፥ ደራሲዎቻቸውም፡ ኢትዮጵያውያን እንደኾኑ አያውቁምን?

እውነተኞቹ ነቢያትና ሓዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታት ኹሉ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት መኾናቸውን አያውቁምን?

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ካልኾኑ በቀር፡ በግብፃዊነት፥ ወይም፡ በእስራኤላዊነት [በይሁዲነት]፥ ወይም፡ በሌላ ማንነት፡ ያን የመሰለውን የተቀደሰ ሙያ ሊፈጽሙ አይቻላቸውም።

አረማዊና ጣዖት አምላኪ የነበረው፡ አብርሃም፡ አምልኮተ-እግዚአብሔርን ላሳወቀውና የግርዛት ቃል-ኪዳንን ላቀዳጀው፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት የበቃው፡ በኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ አስተማሪነት እንደኾነ አያውቁምን?

እንዲሁም፡ በውስጥ ሰውነቱ፡ ዕብራዊ ሣለ፡ በአፍኣዊ ማንነቱ ግን፡ ግብፃዊ ጣዖት አምላኪና አረማዊ የነበረው ሙሴ፡ አምልኮተ-እግዚአብሔርን ላሳወቀውና የታቦተ-ጽዮንን ቃል-ኪዳን ላቀዳጀው፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት የበቃው፡ በኢትዮጵያዊው ካህን ዮቶር አስተማሪነት እንደኾነ አያውቁምን?

በመጨረሻም፡ እስራኤላዊው ንጉሥ ዳዊት፡ በዚያ ማንነቱ፡ እግዚአብሔር የገባለት፡ የዘለዓለማዊውና የመለኮታዊው መንግሥትነት የቃል ኪዳን ዘር፡ ለአማናዊነት ሊበቃ የቻለው፡ በቅድሚያ፡ የኢትዮጵያዊው ኦርዮ ሚስት በኾነችው፥ ኋላም፡ እርሱ ዳዊት፡ ሚስቱ ባደረጋትና ልጁን ሰሎሞንን በወለደችለት፡ በኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ቤትሳባ አማካይነት፥ ቀጥሎም፡ ይኸው ወራሽ ልጁ፡ ንጉሥ ሰሎሞን፡ ኢትዮጵያዊ የበኵር ልጁን፡ ቀዳማዊ ምኒልክን፡ በወለደችለት፡ በኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ አማካይነት ሲኾን፣ ኹለቱም፡ የእስራኤል ነገሥታት፡ በእየራሳቸው፡ ትክክለኛውን አምልኮተ-እግዚአብሔርና የመለኮታዊውን መንግሥት ቃል-ኪዳን ላቀዳጃቸው፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሊበቁ የቻሉት፡ በእነዚህ ኹለት ኢትዮጵያውያት ንግሥታት አስተማሪነት መኾኑን አያውቁምን?

ይህን ኹሉ፡ የእግዚአብሔርን እውነታ ካላወቁ፡ ከዛሬ ጀምሮ እንዲያውቁት ይኹን!

ከዘመነ አዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" የሚያሰኘው ስያሜ፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" በሚለው የተተካ መኾኑ፡ "'አኮ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ አንትሙ በኀቤየ፡ ደቂቀ እስራኤል!' ይቤ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ ስሙ።"

"ስሙ፡ 'ኹሉን የሚገዛ' የኾነ እግዚአብሔር፡ ‹የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።› አለ።" በሚለው፡ በነቢየ-እግዚአብሔር አሞጽ አፍ በተነገረው ቃል ተረጋግጦ ተደምድሟል። (አሞ. ፱፥ ፯።)

የእግዚአብሔር አማኝና ወገን የመኾንን እውነታ፡ እንዲህ አረጋግጦ ሊያሳይና ሊያመለክት የሚችል፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውነት ብቻ እንጂ፡ ግብፃዊነት ቀርቶ፡ እስራኤላዊነት እንኳ፡ ይህን እውነታ ሊያሳይና ሊያመለክት የማይችል መኾኑን፡ ይህን የመሰለው፡ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ሳይኾን፡ "የእስራኤል ልጆች ነን!" የሚሉት፡ የቀደሙትም ኾኑ፥ የዛሬዎቹ አይሁድ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ መሲሕን እስከመግደል ያደረሳቸው የፀረ-እግዚአብሔርነታቸውና የፀረ-ኢትዮጵያነታቸው ግብሮቻቸው ክምችት፡ ይኸው አኹንም፡ በገሃድ እየመሰከረባቸው ይገኛል።

ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ምንነትና ማንነት፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኩል፡ በመጻሕፍታችንና በኀዋ-ሰሌዳችን፥ በፌስ ቡክና በዩ-ቲዩብ፥ በሌሎቹም መድረኮቻችን አማካይነት፡ በሚበቃ የተነገረና የተጻፈ ስለኾነ፡ ያላወቁ ኹሉ፡ እነዚያን መዘክሮች እያገላበጡ እንዲመረምሩ እንጋብዛለን።

\+ + +